

Mercy Housing

# ወደ አዲሱ ቤቶ
# እንኳን ደህና መጡ!

# መግቢያ


የሥራ መጽሐፍ ምልክቶችና ትርጉማቸው i
ተራ እቃዎችና ሥማቸው ii

ወርሃዊ ሂሳቦችን መክፈል 1

አፓርትመንቶን ስለ መንከባከብ
ቤት ከመግባት በፊት ቁጥጥር 2
የመኖርያ አካባቢ 3 5
የአሊጋ ተባዮች 6
ወጥ ቤት
ምግብ አዘገጃጀት 7
ምግብ ስለማፅዳት 8
መቀቀልና መጋገር 9 10
የሳህን ማጠብያ ማሽን 11
ምድጃ 12
የማጠብያ ገንዳና ቆሻሻ መምጠጫ 13
የቆሻሻ ማጠራቀምያ ገንዳ 14
የመጸዳጃ ቤት
አጠቃላይ ጽዳት 15
የሰገራ ገንዳ ችግሮች 16
የውኃ እንጥብጣቢና ፍሳሽ 17
ልብስ ማፅጃ 18

ደህንነትና ጥበቃ
የጢስ ማስጠንቀቂያ 19
እሳት 20 22
ኮሪደሮች 23

ደህንነትና ጥበቃ
የበርና የመስኮት ወንፊቶች 24
የህክምና ኢመርጀንሲዎች 25
ሲጃራ ማጨስ 26
ማሸግያዎች፣ቁልፎች፣የማይታወቁ ሰዎች 27 28

ፓስታና ማስታወቂያዎች
ደብዳቤዎችና የተለጠፉ ማስታወቂያዎች 29
የእድሳት ጥያቄዎች 30

ጥሩ ጎረቤት ስለመሆን
ጫጫታ፣ ችግር መፍታት፣ የቤት እንስሳት 31

የኤለኤክትሪክ ቁተባ
ቴርሞስታት (የአየር መቆጣጠሪያ) 32
ጠቃሚ ምክሮች 33 34

ማጠቃለያ 35


© 2006 በሜርሲ ሃውሲንግ ኢንክ. መብቱ የተጠበቀ. ፍቃድ ለመጠየቅ ወይንም በይበልጥ ለማወቅ ከተፈለገ ለ ሬፍዩጂ ሃውሲንግ ፕሮግራም ሜርሲ ሃውሲንግ ኢንክ. 1999 ብሮድዌይ ስዊት 1000 ዴንቨር ኮሎራዶ 80202 ጥያቄዎን ያቅርቡ።

ይህ መጽሂት የታቀደው ስለ መኖርያ ቤት አጠቃቀም መግለጫ ለመስጠት ሲሆን የኪዝ ማናጅርና የስደተኛ ቤተሰብ ያጠቃልላል። ለብቻው የሚሰራበት ሰነድ ግን አይደለም። ይህ የተጻፈው ዴንቨር ኮሎራዶ በሚገኘው በ አፍሪካ ኮምዩኒቲ ሴንተርና በ ሜርሲ ሃውሲንግ, ኢንክ ትብብር ምክንያት ነው። ስእላዊ መግለጫና ሃሳባዊ ቅየሳ ካሮል ኪምባል ነች ያበረከተችው። የአፍሪካ ኮምዩኒቲ ሴንተርና አርሊንግተን ቨርጂንያ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኮምዩኒቲ ዴቨሎፕመንት ካውንስል (ኢሲዲሲ) ፕሮግራም ነው። ይህ ሰነድ የ ሬፉጂ ሃውሲንግ ሰርቪስስ ፕሮጀክት የቴክኒካል እገዛ የሆነው የ ግራንት ቁጥር 90RB0015 ውጤት ነው። ይህ ግራንት ለሜርሲ ሃውሲንግ, ኢንክ የተሰጠው ከ ሬፉጂ ሪሴትልመንት (ኦርር) ዩኤስ ዲፓርትመንት ኦፍ ሄልዝ ኤንድ ሁማን ሰርቪስስ ቢሮ ነው። በዚህ መጽሂት ውስጥ ያሉት ሃሳቦች የ ኦርርን አስተያየት ሙሉ በሙሉ ላያንፀ


በዚህ የሥራ መጽሄት ውስጥ
የተለያዩ ስእላዊ ምልክቶች
ያጋጥሞታል-ትርጉማቸው
እንደሚከተለው ነው።



ይህ ስእል የኬዞ ማናጀር፥
ማለትም ይህንን መጽሄት
ከእርሶ ጋር በመሆን
የሚይስረዳዎት ሰው
ማለት ነው።

ሥም፡ ______________________


የቴሌፎን ቁጥር፡ ______________




ይህ ሲእል ያከራዩ ሰው ወይንም
የ አፓርትመንቱ ማናጀር ማለት
ነው።

ሥም፡ ______________________

የቴሌፎን ቁጥር፡ ______________





911 በቴሌፎንዎ ቢደውሉ
በቶሎ አገዝ ማግኘት
ይችላሉ። የግል የሆን
አስቸኳ ጉዳይ ሲገጥሞት
ብቻ ይደውሉ።




ይህ “አይ” ማለት ነው
ስእሉ የሚያሳዮትን ነገር
አያድርጉ




ይህ ማለት ገንዘብዎን
ያለአግባብ እያጠፉ ነው።
እነዚህን ነገሮች ላለማድረግ
ይሞክሩ።




ይህንን በየቀኑ ያድርጉ




ይህንን በሳምት አንድ
ጊዜ ያድርጉ





ይህንን በወር አንድ
ጊዜ ያድርጉ

# ተራ እቃዎችና ሥማቸው





ከቤት የማስለቀቅያ
ማስታወቂያ



ሪፍሪጅተር
ፍሪጅ



የቆሻሻ ማጠራቀምያ ገንዳ
የፍሳሽ ቆሻሻ
የተጠራቀመ ቆሻሻ




እሳት ማጥፍያ



ገንዳ
ቧንቧ



የገላ መታጠብያ ገንዳ
ገንዳ




የጢስ ማስጠንቀቅያ



ቴርሞስታት (የአየር መቆጣጠሪያ)



ምድጃ
ቡታጋዝ



የመስኮት ላይ አየር ማቀዝቀዣ
አየር ማቀዝቀዣ




የእቃ ማጠብያ ማሽን




መጸዳጃ



የልብስ ማጠብያ
ማጠብያ ማሽን




የመኒጋገርያ መሳርያ



የእቃ ማጠብያ ገንዳ
ቆሻሻ ማውረጃ

# ወርሃዊ ሂሳቦችን መክፈል




ጥሩ ክሬዲት ለመመስረትና ለመጠበቅ እንዲችሉ በየወሩ የቤት ክራዮን፣ የጥቅመትና ሌላ ክፍያዎን በወቅቱ ይክፈሉ። ጥሩ ክሬዲት ቤት ለመግዛት፣ መኪና ለመግዛትም ሆነ ለኮሌጅ መማርያ ገንዘብ ለመበደር ያግዞታል። የመቆጣጠርያ ቅፅ በመጠቀም የወርሃዊ ክፉያዎን ይቆጣጠሩ።




<u>በፖስታ ጥሬ ብር በምንም አይነት አይላኩ!</u>




# ቤት ከመግባት በፊት ቁጥጥር

እርስዎና የኬዝ ማናጀሮ አፓርትመንቱን ከአፓርትመንቱ ማናጀር ጋር በመሆን የጎደሉና መጠገን የሚያስፈልጋቸውን ነግሮች ማመልከት አለቦት። ይህን ካደረጉ ለቀብድ የሰጡትን ገንዘቦን ቤት ሲለውጡ ለማስመለስ ይችላሉ።






በሳምንት አንድ ጊዜ ምንጣፎን በቫክዩም መምጠጫ ይጥረጉት። ፍሳሾችን ወዲያውኑ በሙቅ ውሃና በሳሙና ያፅዱት። ስሚንቶ መሬቶች በሳምንት አንድ ጊዜ መጠረግ አለባቸው።

ቤት ሲቀይሩ እቃዎች በሙሉ፣ ከመገልገያ ቁሳቁሶች በስተቀር የራሶ ንብረት ናቸው። በደንብ ተንከባክበው ከያዙዋቸው ለብዙ ጊዜ ሊያገለግሎት ይችላሉ። ቤት በሚለቁበት ጊዜ አከራዮ እቃዎን በሙሉ ይዘው እንዲወጡ ይጠብቃል። የትኞቹን እቃዎች መውሰድ እንደሚችሉ ለማወቅ ከፈለጉ ኮንትራቶን ያንብቡ ወይንም ኬስ ማናጀሮን ያነጋግሩ።

ወደ አፓርትመንቶ ሲገቡ ጫማዎን ያውልቁ። ይህ ምንጣፎን በፅዳት ለመጠበቅ ያግዞታል።









ምንጣፍ ላይ ፈሳሽ ነገር አያፍስሱ። ወደ ውስጥ ጠልቆ ከገባ ለማስለቀቅ የሚያስቸግር ጉድፍ ይተውበታል።



ፍሳሾችን ወዲያውኑ ይጥረጉ!
የኤሮሶል ምንጣፍ መጥረጊያ ከግሮሰሪ በመግዛት ይጠቀሙ።



ፈጽመው በረኪና ምንጣፍ ላይ አይጠቀሙ!



ጉድፍ አለቅ ብሎ ካስቸገሮት ኬዝ ማናጀሮን ምክር ይጠይቁ።



ልጆችን መጋረጃ ውስጥና በመስኮት መሸፈኛዎች ውስኅ **እንዳይጫወቱ** አስተምሩ። ግርግዳ ላይ **እንዳይፅፉም** አስተምሩዋቸው።



በጣም ከበድ ላለ ጉድፍ የምንጣፍ ማጠብያ ማሽን ከግሮሰሪዎች መከራየት ይችላሉ።

ልጆችን በአፓርትመንቶ ውስጥ ስላሉ ነገሮች ጥንቃቄ እንዲወስዱ አስተምሩ። በእቃ ላይ እንዳይንጠላጠሉና እንዳይዘሉ **ተቆጣጠርዋቸው**።



## የአልጋ ተባዮች



የአልጋ ተባይ ንክሻ ያበጠና ቀላ ያለ ነው።



<u>በምንም</u> ዓይነት መንግድ ላይ የተገኘ እቃ ወደ ቤቶ አያስገቡ።





የአልጋ ተባዮች በጨርቅ እጥፋት ውስጥ፣በግርግዳ ጠርዝ፣በምንጣፍና በአልጋ ልብስ ውስጥ ይኖራሉ። የአልጋ ተባዮች ካገኙ የአልጋ ልብሶን በሙቅ ውሃና በሳሙና አጥበው በሙቅ ማድረቅያ ያድርቁት። ፍራሽ፣የቤት እቃ፣ምንጣፍና፣ የግርግዳ ጠርዞችን በቫኪውም መጥረጊያ ጠርገው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከረጢቱን ወዲያውኑ ወድ ውጭ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ወስደው ይጣሉት።

አልጋና ሶፋዎችን ከግርግዳ ራቅ ያድርጉዋቸው። መሸፈኛዎችን መሬት እንዳይነኩ አድርጉ። በአልጋ እግሮች ስር ፈሳሽ ሳሙና ያለበት ቆርቆሮ ያስቀምጡ።

## ምግብ አዘገጃጀት



የወጥ ቤቱን የእቃ ማስቀመጫ ካበላሹ ክፍለው ማሰራት ይኖርቦታል። በቢላዋ ሲጠቀሙ የእንጨት መክተፊይ ላይ ይቁረጡ።







<u>በምንም ዓይነት</u> በወጥ ቤቱ የእቃ ማስቀመጫ ላይ አትቁረጡ!




በምንም ዓይነት መሬቱ ላይ አትቁረጡ!

<u>በምንም ዓይነት</u> የጋለ ድስት በወጥ ቤቱ የእቃ ማስቀመጫ ላይ በትክክል አያስቀምጡ!

ከድስቱ ስር የሙቅ እቃ ማስቀመጫ ወይንም ደረቅ ጨርቅ ይጠቀሙ።



## ምግብ ስለማፅዳት




የወጥ ቤቱን የእቃ ማስቀመጫ
በየቀኑ ያፅዱት።









በምንም ዓይነት ምግብ ሳይከደን የወጥ
ቤቱ የእቃ ማስቀመጫ ላይ አይተውት።
ይህ ትላትልና አይጦች ሊያመጣ ይችላል።
<u>ይህ ከሆነ የተባይ ተከላካይ ባለሞያዎች
ከፍለው ችግሩን ማስወገድ ይኖርቦታል!</u>

ምግቦ ምግቦችን ሁልጊዜ መሸፈንና በማቀዝቀዣ ውስጥ
ማስቀመጥ ይመረጣል። የማቀዝቀዣውን ውስጥ በየጊዜው
በሳሙናና በውሃ ይጠቡት።
ቤት ሲቀይሩ ማቀዘቀዣው <u>ንፁህ ካልሆነ ተጨማሪ ገንዘብ
መክፈል ይኖርቦታል!</u>



## መቀቀልና መጋገር

ምድጃ ላይ ምግብ ሲቀቅሉ ሁልጊዜ በመካከለኛው የእሳት መጠን ይጀምሩ። በከፍተኛው ፍም መቀቀል ከጀመሩ ምግቡን አሳርረው ድስቱንም ያቃጥሉታል። የድስቱን ታችም ሊያቃጥሉት ይችላሉ።












የጋለ ማንደጃና የምድጃ ጉልቻ ሊያቃጥሎት ይችላል!

ምድጃ ላይ የነበሩ ድስቶችና ሳህኖች በደረቅ ጨርቅና በእቃ መያዣ ጨርቅ ያንሱ።

## መቀቀልና መጋገር




ምግብ ለመቀቀልና ለመጋገር ሲፈልጉ በምድጃውን 350 ላይ ያድርጉት ወይንም የአሰራሩን መመርያ ይከተሉ። ምድጃውን እስከ መጨረሻ ድረስ መክፈት ምግቦን ያቃጥልቦታል። ማንኛዎቹንም ፍሳሾች ምድጃው እንደቀዘቀዘ ወዲያውኑ ይፅዱት።







የምድጃው ፍም ላይ ምግብ አይቀቅሉ!

## የሳህን ማጠብያ ማሽን

የእቃ ማጠብያ ማሽን በሳህንና በብረታ ብረት ላይ ሊገኙ የሚችሉ ህዋሳትን የገድላል።እቃዎችን ግን የመሬ ፈግና ቆሻሻ የማስወገድ ችሎታ ግን የለውም። ሁልጊዜ የምግብ ፍርፋሪዎችን ጠርገው ወድ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ በማራግፍ ሳህኑን ይለቅልቁት፣ከዚያ ወደ እቃ ማጠብያ ማሽን ውስጥ ያስገቡት። ለእቃ ማጠብያ ማሽን ለብቻው የተሰናዳ ሳሙና ብቻ ይጠቀሙ። ሃይለኛ ስለሆነ ከሚገባው በላይ አ ይጨምሩ። በምንም ዓይነት ፈሳሽ ሳሙና ወይንም የልብስ ማጠብያ ሳሙና እቃ ማጠብያ ማሽን ውስጥ አይጨምሩ። መሬቱን በየቀኑ ይጥረጉና በሳሙናና በውሃ በየሳምንቱ ይወልውሉ።



## ምድጃ




የቅባትና የምግብ ፍሳሾች <u>**ወድያውኑ**</u> ይጥረጉ፣ምድጃዎንም በየቀኑ ያፅዱ።






ቅባት በእቃ ማጠብያ ገንዳ ውስጥ አያፍስሱ። ባዶ ቆርቆሮ ውስጥ በመገልበጥ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ይጣሉት።



የፈሰሰ ወይንም የተቃጠለ ምግብ ወይንም ቅባት አደገኛ ነው። መጥፎ ሽታ ስለሚያመጣ ትላትልና አይጥ ይጠራል።
<u>የፈሰሰ ቅባት ሊያዳልጥ</u> ይችላላ!
<u>የፈሰሰ ቅባት እሳት ሊፈጥር ይችላላ!</u>




## የማጠብያ ገንዳና ቆሻሻ መምጠጫ



አጥንት፣የእንቁላል፣የአታክልት፣የሽንኩርት፣የሰሊሪ ልጣጭና ብረታ ብረት የማጠብያ ገንዳና ቆሻሻ መምጠጫ ውስጥ አይጣሉ።








ቤቶ ምግባ ምግብ የሚፈጭ የቆሻሻ መምጠጫ ሊኖረው ይችላል። ሁልጊዜ የቆሻሻ መምጠጫ ሲጠቀሙ ቀዝቃዛ ውሃ ያፍስሱ።

የቆሻሻ መምጠጫው ከተደፈነ የእቃ ማጠብያ ገንዳው ውስጥ ውሃ ተመልሶ ይሞላል። አጥፍተው የአፓርትሙቱን ማናጀር ይጥሩ። በምንም ዓይነት እጅን በቆሻሻ መምጠጫው ውስጥ አይክተቱ

## የቆሻሻ ማጠራቀምያ ገንዳ




የተጠራቀመ ቂሻሻ በአፓርትመንቶ ውስጥ በተሰናዳው የቆሻሻ ማጠራቀምያ ገንዳ ውስጥ ይጣሉ። በፕላስቲክ የቆሻሻ ከረጢት ያድርጉት።
የተጠራቀመውን ቆሻሻ የቆሻሻ ማጠራቀምያ ገንዳ ውስጥ በየጊዜው ይውሰዱ። የቆሻሻው ጠረን ትላትልና አይጦች ስለሚያመጣ ጎረቤቶችዎ ለአፓርትመንት ማናጀሩ አቤቱታ ያቀርቡቦታል።
<u>በምንም ዓይነት</u> ቆሻሻ በአፓርትመንቱ ኮሪደር ላይ አይተው።



በአካባቢዎ የሪሳይክሊንግ ፕሮግራም ካለ ስለአሰባሰቡ የሚሰጥዎትን መመርያ ይከተሉ።







## አጠቃላይ ጽዳት

የመጸዳጃ ቤት በየሳምንቱ መፅዳት አለበት። ይህም ወለሉን፥የሰገራ ገንዳውን፥የፊት መታጠቢያውን፥የገላ መታጠቢያውና የሻወሩ ውጭና ውስጥ ያጠቃልላል።

ፀጉርና የመሳሰሉትን ነገሮች ወደ ውሃ መሄጃው ውስጥ አይጣሉት።











## የሰገራ ገንዳ ችግሮች



በየሳምንቱ የሰገራ ገንዳውን እግር ውስጥና ውጭ ይጥረጉት። ሽንት ሲፈስ ወዲያውኑ ወለሉን ይጥረጉት።

<u>የሰገራ ገንዳዎ ሞልቶ ከፈሰሰ ወዲያውኑ የአፓርፍትመንቱን ማናጀር ይጥሩ!</u>





በምንም ዓይነት የሴቶች የሚጠቀሙበትን ፓድ፥ቆሻሻ፥ምግብ፥የመፀዳጃ ወረቀትና በዛ ያለ የሽንትቤት ወረቀት እንዲሁም ሌላ እቃዎች ሰገራው ገንዳ ውስጥ አይጣሉ።

<u>ልጆችዎን መጫወቻችና ሌላ እቃዎች የሰገራ ገንዳ ውስጥ እንዳይጥሉ አስተምሯቸው።</u>



የሰገራ ገንዳውን ቡሩሽ በመጠቀም ይጠቡት።

<u>የሰገራ ገንዳ ማጠቢያውን ቡሩሽ ለሌላ ነገር በምንም ዓይነት እንዳይጠቀሙ!</u>

## የውኃ እንጥብጣቢና ፍሳሽ

ሁልጊዜ የሻወሩን መጋረጃ በገንዳው ውስጥ በኩል ያድርጉት፤ውሃ ከፈሰሰም ቶሎ ብለው ወዲያውኑ ይወልውሉት። በገንዳው ውስጥ የማያንሸራትት ምንጣፍ ማድረግ ከመውደቅ ይከላከላል።


ገንዳው ተዘግቶ ውሃ አልሄድ ካለ ወይንም የምያፈስ ቀዳዳ ከተፈጠረ የአፓርትመንቱንማናጀር ወዲያውኑ ይጥሩ!

ካልሆነ ግን ላላመለከቱት የውሃ ፍሳሽ ብልሽት መክፈል ይኖርቦታል።









## ልብስ ማፅጃ

1. ልብሶችን ነጣ በሚሉና ጠቆር በሚሉ ይለያዩዋቸው።
2. ሙቅ እጥበትና ቀዝቃዛ እጥበት የሚለውን ይጠቀሙ። ወይንም ከልብሱ ውስጥ ያለውን መመርያ ይከተሉ።
3. መጀመርያ ማሽኑን ያስነሱና ሳሙናውን ያስገቡ፤ ከዚያ ልብሱን ይጨምሩ።
4. ብዙ ልብስ በማጠብያውም ሆነ በማድረቂያው ውስጥ አያጭቁ።
5. ከማድረቅያው ውስጥ ያለውን የቡናኝ ማጠራቀሚያ ሁልጊዜ ይጥረጉት።
6. ልብሶን ሳይጠብቁ አይተውት።



# የጢስ ማስጠንቀቂያ

በአፓርትመንቶ ውስጥ አከራይዎቹ የጢስ ማስጠንቀቂያ መሳርያ ማስገባት አለባቸው። የጢስ ማስጠንቀቂያ ድምፁ መሥራት አለበት። ሂይወቶን ሊያድን ይችላል።

<u>የጢስ ማስጠንቀቂያ ማሽኖ ባትሪ ካለው በትክክል መሥራቱን ማረጋገጥ አለቦት። በዓመት አንድ ጊዜ</u> መለወጥ አለበት። ለእርሶ <u>ትርጉም ሊኖረው የሚችል</u> ቀን ይምረጡ!



የጢስ ማስጠንቀቂያ መሳርያዎን እፊቱ ላይ የሚገኘውን ቁልፍ በመጫን መሥራቱን ያረጋግጡ። የጢስ ማስጠንቀቂያው ድምፅ ከሎኸ እንደገና ቁልፉን በመጫን ያጥፉት።





<u>በምንም ዓይነት የጢስ ማስጠንቀቂያ መሳርያውን ከቦታው አያውጡት ወይንም አይግለጡት!</u>

የጢስ ማስጠንቀቂያ መሳርያው የማይሠራ ከሆነ የአፓርትመንት ማናጀሮን በአፓርትመንት ህንፃ ውስጥ የእሳት ማጥፍያ መሳርያ የተቀመጠው የት እንደሆነ በደንብ ይወቁ፤አጠቃቀሙንም ይማሩ።





**በምንም ዓይነት ክቅባት በተነሳ እሳት ላይ ውሃ አይርጩበት!**

WXYZ 9 1 1

Medical Fire Police

1 እሳቱ ትንሽ ከሆነ በሌላ መጥበሻ ወይንም መክደኛ በመሸፈን ለማጥፋት ይሞክሩ።

2. እሳቱ በጣም ትልቅ ከሆነ በተማሩት መሠረት የእሳት ማጥፊያው መሳርያ ያጥፉት። አንድ ጊዜ ከተጠቀሙበት በኋላ የአፓርትመንቱ ማናጀር መሳርያውን እንደገና መሙላትና ለሚቀጥለው ጊዜ ሲፈልጉት ዝግጁ ሁኖ እንዲቆይ ማድረግ አለበት።


3. እሳቱን ማጥፋት ካልቻሉ ግን

ሰዎቹን በሙላ ከህንፃው አስወጥተው 911 ይደውሉ!

የሰው ሂወት ከእቃ በላይ ነው!








እሳቱ በጣም ትልቅ ከሆነ ደግም 911 ይደውሉ! ከቻሉ ወደ ውጭ ይውጡ። ከጭሱ በታች ዝቅ በማለትና ጭሱን ላለመተንፈስ ይሞክሩ። ከቻሉ ጎረቤቶችን ለማሳወቅ ይሞክሩ። በምንም ዓይነት ከእሳት ለማምለጥ ወደ ኤሊቬተር አይግቡ። ደረጃዎቹን ይጠቀሙ።




በራፎ ከጋለ አይክፈቱት። ለመሬት ቅርብ የሆነ መስኮት በመጠቀም ለመውጣትና እሳቱን ለማምለጥ ይሞክሩ፣ ወይንም መስኮት አጠገብ በመቆም እርዳታ እስኪመጣ ይጠብቁ። በእርጥብ ጨርቅ ላይ ይተንፍሱ።






ኮሪደሮችና በጋራ የመጠቀሚያ አካባቢዎች በግልጽ ካልተያዙ አደገኛና በፍጥነት ለማምለጥ በሚፈልጉበት ጊዜ መሰናክል ሊሆን ይችላል።



በጋራ የመጠቀሚያ አካባቢዎችን በንፅህናና ከአደጋ ነፃ በሆነ መንገድ መጠበቅ ከጎረቤቶች ጋር በስምምነት ለመኖር ይጠቅሞታል።




የበርና የመስኮት ወንፊቶች ልጆችና እንስሶችን እቤት ውስጥ ለመያዝና ትላትልና ህዋሳትን እንዳይገቡ ለማገድ ይጠቅማል።

ወንፊቶቹ ከተቀደዱ ውይንም ከሌሉ የአፓርትመንት ማናጀሩን ይጥሩ።










**አንድ ሰው በጠና ከታመመ 911 ይደውሉ!**

የሚያድኑ ሰዎች ወድያውኑ መጥተው ሊይግዞት ይችላሉ።
ችግሩን ካወቁ በኋላ አንቡላንስ የሚያስፈልግ

ከሆነና ወድ ሆስፒታል መሄድ የማያስፈልግ ከሆውነ ለመወሰን ያግዞታል።

መክፈል የሚይስፈልጎት አንዳንድ ነገሮችም ሊኖሩ ይችላሉ።







የአሜሪካን ሲጃራዎች ባያጨሱትም መንደዱን ይቀጥላል።
ሁልጊዜ ሲጃራ ከመጣሉ በፊት መንደዱን ማቆሙን ያረጋግጡ።

በአፓርትመንቱ ውስጥ ለተቃጠሉ
ቦታዎች እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ።





አልጋ ላይ ተኝተው ወይንም እንቅልፍ ሊወስዶት የሚችልበት
ቦት ላይ ሁነው አያጭሱ።




በልጆችና በእርጉዝ ሴቶች አካባቢ አያጭሱ።



አዋቂ ሰዎችም ሆኑ ልጆች ለማያውቁት ሰው የበር ቁልፍ መክፈትም ሆነ በኢንተርኮም ሰው ማስገባት የለባቸውም።






**ሰዎች ሲሰርቁ ካዩ 911 ይደውሉ!**

ሁልጊዜ በሮን ይቆልፉ፤እቤት ውስጥ ቢሆኑም። ለደህንነት ከቤት ከመውጣቶ በፊት መስኮቶቹን ዘግተው ይቆልፉዋቸው።



የማያውቋቸውን ሰዎች በሎቢው ውስጥ ተከትለዎት እንዳይገቡ ይጠንቀቁ።



ቁልፎን ከረሱና ወደ ቤቶ መግባት ካልቻሉ $50.00 ወይንም የበለጠ ከአከራዩ በሩን እንዲከፍትሎት መክፈል ይኖርቦታል። ቁልፎን ካጠፉ በሌላ ለመተካት ብዙ ገንዘብ ሊያስወጣዎት ይችላል።







ወደ ቤትዎ ከማስገባትዎ በፊት ማንኛውንም የማይውቁትን ሰው መታወቂያ ወረቀት እንዲያሳይ ይጠይቁ። ዩኒፎርም የለበስ ቢሆንም።



ደብዳቤዎችንና ጠቃሚ ወረቀቶችን በጥንቃቄ ያንብቡና ደህና ቦታ ያስቀምጡ።

ያልገባዎት ነገር ካለ የኬዝ ማናጀሮን በመደወል አገዝ ይጠይቁ።



የፖስታ ሣጥኖን በየቀኑ ይፈትሹ። የማይስፈልጉ ደብዳቤዎችን በሎቢው ወለል ላይ አይጣሉ።








በራፎ ላይ አንድ ማስታወቂያ ከተለጠፈ ወዲያውኑ መልስ ይስጡ። ቤት የማስለቀቅያ ማስጠንቀቅያ የሚሰጠው በዚህ ዓይነት ነው።

# የእድሳት ጥያቄዎች



አከራዮች ብዙ ጊዜ እድሳት ከማድረጋቸው በፊት በፅሁፍ ጥያቄ እንዲቀርብላቸው ይፈልጋሉ። የእድሳት መጠየቂያ ቅጽ ይጠቀሙ፣ ወይንም ኬዝ ማናጀሮን አገዝ ይጠይቁ።

www.refugeehouse.org ከተባለው ዌብ ሳይት የእድሳት መጠየቂያ ቅጽ ማግኘት ይችላሉ።








ሰገራ ቤቱ ተደፍኗል።



ምድጃየ አይሰራም።



የቆሻሻ መምጠጫየ አይሰራም።



ቧንቧየ ውሃ ያፈሳል።




ወንፊቶቹ መሠራት ያስፈልጋቸዋል።

ብዙ ሰዎች ወደ 10፡00 ሰዓት አካባቢ ነው የሚተኙት። ልጆችን ፀጥ እንዲሉ አድርጉ። ንግግሮን ቀነስ ያድርጉ፣ ጮክ ያለ ሙዚቃም በምሽቱ 10 ፒም ና 8 ኤም አያጫውቱ።


ጫጫታን በሚመለከት አከራዩ ያወጣውን መመርያ ይከተሉ። መመርያው በኮንትራቱ ውስጥ ይገኛል።







ከጎረቤቶች ጋር አለመግባባት ቢፈጠር ከነሱ ጋር በመነጋገር ለመፍታት ይሞክሩ። ካልቻሉ ግን ከ ኬስ ማናጀሮ ወይንም ከ አፓርትመንት ማናጀሮ እገዛ ይጠይቁ።



እንዳንድ አፓርትመንቶች የቤት እንስሳዎች ለማስገባት ይፈቅዳሉ። የትኞቹ የቤት እንስሳዎች እንደሚፈቀዱ ያጣሩ።



## ቴርሞስታት (የአየር መቆጣጠሪያ)

ቤት ተከራዮች ቡዙ ጊዜ ለማሞቅያ፥ለኤሌክትሪክና ለአየር ማቀዝቀዣ ይከፍላሉ። እነዚህ ውድ ሊሆኑ ይችላሉ። የወርሃዊ ወጭዎን ለመቀነስ የሚከተለውን መመርያ ይከተሉ።

ቴርሞስታቱ በአፓርትመንቶ ውስጥ ያለውን ዓየር ይቆጣጠራል። በክረምት በ 65ና በ 75 ዲግሪ ላይ መሆን አለበት። በበጋ ደግሞ ከ70 እስከ 75 ዲግሪ ላይ መሆን አለበት።



ቴርሞስታቱን ሁልጊዜ ከፍ ማድረግ አየሩን ይበልጥ ከፍ አያደርገውም ። ከዚያም በላይ ወደታች ከመቀነስ ከረሱ በጣም ብዙ ገንዘብ ሊያስከፍሎት ይችላል።






አየር ማሞቅያውም ሆነ አየር ማቀዝቀዣው በተከፈተበት ጊዜ መስኮቶች መዘጋት አለባቸው!



ሁልጊዜ መብራቶችናን የመዝናኛ መሳርያዎችን ከቤት ሲወጡ ያጥፉዋቸው። አንድ ወይንም ሁለት መብራቶች ግን እንዳበሩ ይተዋቸው፣ ሌቦች እቤቱ ውስጥ ሰው ያለ ይመስላቸዋል።



**በምንም ዓይነት ማሞቂያው ተከፍቶ ከሆነ መስኮቶችን አይክፈቱ!**

አየር በተዘጉ በራፎችና መስኮቶች እያለፈ የሚሰማዎት ከሆነ አከራዮን ቀዝቃዛ አየር ከመግባት የሚከላከል ነገር እንዲያስገባሎት ይጠይቁ።







ካልሲ፥ረጅም ሱሪና እጅጌ ያለው ልብስ መልበስ ወይንም ደራርበው መልበስ ሙቀት ሊሰጡት ከመቻሉም በላይ ሙቀቱን ከፍ ከማድረግ ይልቅ ረከስ ይላል።



በምንም ዓይነት ምድጃውን ውይንም መጋገሪያውን ለሙቀት አይጠቀሙ!







የማቀዝቀዣውን በር በተቻለ መጠን ሁልጊዜ ይዝጉት። በሩን ከፍቶ መተው ኤሌክትሪክ ከምባከኑ በላይ ምግቦች እንዲበላሹ ስለሚያደርግ ለበሽታ ሊዳርጎት ይችላል።

# ማጠቃለያ


1. ወርሃዊ እዳዎን ይክፈሉ።
2. ነገሮችን በንፅህና ይያዙ።
3. ንብረቶችን ተንከባክበው ይያዙ።
4. እሳትና የመሳሰሉትን አደጋዎች እንዴት እንደምትከላከሉ ይወቁ።
5. ደብዳቤዎችንና ማስታወቂያዎችን ያንብቡ።
6. ጥሩ ጎረቤት ይሁኑ።
7. የአገልግሎት ሃይልን አያባክኑ።



ንብረቶችን ተንከባክበው ይያዙ።



ወርሃዊ እዳዎን ይክፈሉ።




ጥሩ ጎረቤት ይሁኑ።



እሳትና የመሳሰሉትን አደጋዎች እንዴት እንደምትከላከሉ ይወቁ።



ነገሮችን በንፅህና ይያዙ።



የአገልግሎት ሃይልን አያባክኑ።



ደብዳቤዎችንና ማስታወቂያዎችን ያንብቡ።

የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ተባባሪዎች፣
ጀኒፈር ጉዌዲቿ፡ የአፍሪካ ኮምዩኒቲ ሴንተር ፕሮግራም ዲሬክተር፣ስኮት ሮቢንስ የሬፉጂ ሃውሲንግ ፕሮጀክት ማናጀር - ለሜርሲ ሃውሲንግ፣ካሮል ኪምቦል አርቲስት - ከሰልጣኞች ጀኒፈር ሃርደንና ባራ ቴኖር.

Mercy Housing

1999 Broadway, Suite 1000 Denver, CO 80202
Phone 303.830.3300 Fax 303.830.3301
www.mercyhousing.org www.refugeehouse.org

Amharic 1106